




## የዘመነ መንደርተኛነት የመጨረሻው ምዕራፍ! (ቁጥር 3)

## “ምርጫው ወደ ቅርጫ ከተለወጠ” ሊከሰት የሚችለው የማንሸሸው ሃቅ!

ብስራት ኢብሳ (ሆላንድ) **26/1/2020**

እንደ ልማድ ሆኖብን በሀገራችን ባህል መጪውን ሁኔታ (scenario) በበጎ ጎኑ መተንበይ እንጂ፣ ሊሆን የሚችለውን መጥፎ ጎን ማሳየት እንደ “ሟርተኛ” ያስፈርጃል፡፡ በባህላችን “ያልጠረጠረ ተመነጠረ” አይነት አባባል ቢኖረንም፣ የጠረጠርነውን መራራ ሃቅ በውስጣችን ደብቀን፣ ሰዎች ሊሰሙ የሚፈልጉትን ደግ ደጉን ነው የምንነግራቸው፡፡ አንዳንድ ደፈር ብለው የተሰማቸውን ስጋት ለማሳየት የሞከሩትን እንደ ቅዠት ተሞክሮ (hallucination) አስተናጋጆች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ እኛ ሊሆን የሚችለውን እውነት ስለተናገርን ብቻ የሚፈጽ የሚመስላቸው ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ ይህ መጥፎ ልማድ ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ቀድሞ በመገመት በጊዜ መፍትሄ ለመፈለግ ዝግጅት እንዳይደረግ ያዘናጋል፡፡

ከዚህም ምክንያት በመነሳት፣ በወቅቱ በሀገራችን ስለሚካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ፣ ብዙ አስተያየቶች እየተሰጡ ቢሆንም፣ ምናልባት እኔንም ሟርተኛም ሊያስብለኝ የሚችል ስጋቴን ለማካፈል ስሞክር፣ ብዙዎች ሃሳብ ውስጥ ያለውን ስጋት ከፈትፈት ለማድረግ እንጂ የማታውቁትን ነገር ልጽፍ አይደለም፡፡

የወያኔ አስተዳደር በቋንቋና ብሔር ከፋፍለው በመንደር ካካለሉን ቦኋላ፣ ወጤቱ በሕዝባችን መሃከል ለዘመናት የተገነባውን አብሮነት አደጋ ላይ ጥሎታል፡፡ ዘርን እና ኃይማኖትን ከፖለቲካ ጋር እየለወሱ ሕዝብን በመከፋፈል ስልጣን ለመያዝ ለሚፈልጉ ጽንፈኛ ምሁሮች የተመቻቸ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል፡፡

እነዚህ የአክራሪ ብሔርተኛ መሪዎች፣ ትምህርት ጨርሶ ስራ በማጣት የተቀመጠውንም ሆነ ሰንፎ የሚያውደለድለውን ወጣት በአክራሪ ብሔርተኛ አስተሳሰብ እያጠመቁ በመመልመል፣ የነሱ ዓላማ ማስፈጸሚያ ጀሌ አድርገው፣ ብዙዎችን መጀመርያ የዛሬ ሁለት ዓመታት ግድም ይዘው ከተነሱበት ዓላማ ጠልፈው አቅጣጫቸውን አስቀይረዋቸዋል፡፡

የእምነት ተቋሞቻችንን በየቦታው በእሳት እየጋየ፣ ፈጣሪን በጋራ ለማመስገን ሰብሰብ ሲባል በድንጋይና በገጀራ የሚወግርህ የነዚህ ጽንፈኛች ጀሌዎች በየከተማው ተባዝተዋል፡፡ ለዘመናት በየዓመቱ የምናከብራቸውን የኃይማኖት በዓላትን እንኳን ማክበር የተሳነባት ምድር እየሆነች ነው፡፡ ካካባቢው ብሔር ያልተወለዱ ወገኖቻን በደህና ጊዜ እራሳቸውን ጠቅመው ለአካባቢውም ስራ በመፍጠር የገነቧቸው ንብረቶች እየተዘረፉና እየተቃጠሉ፣ መጤ እየተባሉ ባሳፋሪ ሁኔታ እያሳደዱ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ መግደል በተለያየ ክልል ባለፉት ጊዜያት በግልጽ እየታየ ነው፡፡

የመኪና ጎዳናዎች ሕግ የማስከበር የትራፊክ ስራ የፖሊሶች መሆኑ ቀርቶ በቡድን በየአካባቢው በህገወጥ በተደራጁ ስራፈት ወጣት ወሮበሎች ተነጥቀው ሰዎች በሰላም ወጥተው መግባት በጣም አዳጋች የሆነበት ወቅት ነው፡፡ ባጭሩ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ችግሮች በሚካሄድባት ሀገር፣ ስለ ሰላማዊ፣ ሕጋዊና ፍትሃዊ ምርጫ ሲነገር በስፋት ይደመጣል፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች ዓላማቸውን ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ለሕዝብ እንዴት ነው የሚያሳውቁት?፡፡ በየቦታው ያለው መራጭስ እንዴት ነው ደፍሮ ስብሰባ የሚጠራው? ማነውስ ደፍሮ ከሌላ አካባቢ ለመጣ ድርጅት የስብሰባ አዳራሽ የሚያከራየው? ስብሰባስ ገብቶስ ውይይት የሚያደርገው? ሳይፈራ የሚጠይቅና የሚያምንበትን ተከራክሮ ፍላጎቱን በነጻ ምርጫ የሚወስነውስ?፡፡

እንደ የከፍተኛ ትምህርት ወጣት ተማሪዎቻችን፣ ከየተሰማሩበት አካባቢ ተጠልፈው  እየታፈኑ ወደ ጫካ ላለመወሰዳቸው? ላለመደብደባቸውና ላለመገደላቸው ምን ዋስትና አላቸው? ማን ሃላፊነትስ ይወስዳል? አሁን የሌለ የደኅንነት ዋስትና ነገ በተአምር ከየት? እንዴት ይመጣል?፡፡

ያውም ችግር ፈጣሪዎቹ በአካባቢ ፖሊስና ደህንነቶች ድጋፍ እየተሰጣቸውና፣ መንግሥትም “መራጮቹን ላለማስቀየም ባደባባይ የሚታዩ ችግሮችን “ጆሮ ዳቦ ብሎ” አቋም የወሰደ እስከሚመስል ጸጥ ባለበት ሁኔታ፡፡ የጸጥታ አስከባሪዎቹ ምን ያህሉ ከአካባቢው የፖለቲካ ወገናዊነት ገለልተኛ ናቸው?፡፡ የጸጥታ አስከባሪዎቹና መጠነ ሰፊ የሆነው የየክልሉ ታጣቂ ሚሊሻ ከአካባቢው ባለስልጣኖችና ፖለቲከኞች ተጽእኖ እውነት ነጻ ናቸው? የመሳሰሉት ጥያቄ መልስ ይሻሉ፡፡

<u>በተለይ አብዛኛዎቹ መራጮች ከጎሊናቸው አስቀድመው ብሔራቸውንና ኃይማኖታቸውን ከመረጡ፣ የሀገራችን ሁኔታ ሁለተኛ ወደነበረበት እንዳይመለስ ሆኖ ሕጋዊ እውቅና ተሰጥቶት፣ ከመካከለኛው ዘመን ቦኋላ እንደተፈጠረው አይነት የአካባቢ ነገሥታት እንደገና “በምርጫ” ህልውናቸው ይረጋገጣል፡፡</u>

<u>በተለይ በዜግነት (አንድነት)የሚያምነው ክፍል አሁን እንደሚታየው ተዘናግቶ፣ እርስ በርስ እየተጠላለፈ ብቻውን መሮጥ ቀጥሎ ተበታትኖ ከተሸነፈ አደጋውን ያፋጥነዋል፡፡</u>

ብዙዎች ይደርሳል ብለው መቀበል ቀርቶ ማሰብ እንኳን የሚፈሩት፣ በሀገራችን አይተነው የማናውቅ ሌላ አዲስ የአስቀያሚ የታሪክ ምዕራፍ ሊከፈት ይችላል፡፡ ከእርስ በእርስ  ጦርነትና የመበታተን አደጋ ሀገራችን ልታመልጥ አትችልም፡፡ እንደእዛ አይነት ሀገራዊ ምርጫ መድረሻ ውጤቱ የሚደመደመው፣ ለመለያየት በጽሁፍ ያልተቀመጠ፣ ነገር ግን በመግባባት በጓሮ በር የተደረሰ የጋራ ስምምነትን ነው የሚሆነው፡፡

ሀገራችን እና ዲሞክራሲ እስከ ወዲያኛው አደጋ ላይ መውደቃቸው ብቻ ሳይሆን፣ ለዘመናት አስተሳስረው ያኖሩን ድልብ የታሪክና የአብሮነት....ወዘተ እሴቶቻችን እስከመጨረሻው ሊያመልጡን ይችላሉ፡፡ ብዙ ከውድ ሀገራችን <u>ከኢትዮጵያ ስም</u> ጎን ተጋምደው የኖሩ፣ በብሔራዊና በዓለም አቀፋዊ መድረክ የምንታወቅበት የማንነትና የብዙ ነገር መለያችንን ወደየመንደራችን ስሞች በፍጥነት እየተቀየሩ ናቸው፡፡

ጉዞዋችን በዚህ ቀጥሎ በጊዜ እርምት ካልተደረገ! አሁን የምናቃትን ኢትዮጵያን እና የኢትዮጵያን ካርታ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ “ሕገመንግስት”፣ ፕሬዘዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ ኤንባሲዎች፣ አየር መንገድ፣ ፓርላማ፣ ዳኛ፣ ሕግ አስከባሪ፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋች፣ ብሔራዊ ጦር፣ ብሔራዊ እስፖርት፣ ብሔራዊ በዓላት፣ ሕግና፣ ባንኮች... ከስማቸው በፊት ኢትዮጵያ ያለበት ነገር ሁሉ፣ ወደ መንደር (ክልል) ስሞችና የክልል ባንዲራዎች ይቀየራሉ፡፡ ምናልባት በዛ ስም የምናውቃቸው የመጨረሻዎቹ እኛ እንዳንሆን እሰጋለሁ፡፡

ባንኮች ኢንሹራንሶችና ሕዝባዊ የሙያና የሲቪክ ማኅበራት ሳይቀሩ አንዳንዶቹ አሁንም ተቀይረዋል፡፡ በብሔራዊ ደረጃ የምንታወቅባቸው መለያዎቻችን እየፈራረሱ የየብሔሮቻችንን ስም እየተተኩ ነው፡፡ በሚያሳፍር መልኩ በዓለም አቀፍ የእስፖርት ውድድር ሳይቀር የምንታወቅበት ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችን በክልል ባንዲራዎች በፍጥነት እየተቀየሩ ነው፡፡ ይህን አደገኛ አካሄድ፣ መንግሥትም የተስማማበት እስከሚመስል እርማት ሳያደርግ፣ እኛም በሂደት ጆሮዋችንና ዓይናችን እየለመደው ነው፡፡

ከምርጫው ቦኋላ በሚፈጠረው ቀውስ የእያንዳንዱ ሰላማዊ ዜጋ ሕይወትን ችግር ውስጥ የሚከቱ ቀውሶች በፍጥነት እያደጉ እንደሚመጡ አንርሳ፡፡ አንዱ ችግር ለሌላው አቀጣጣይ ቤንዚን ነውና!፣ የምግብና የውሃ እጥረት፣ የእቃ ዋጋ መናር፣ የቤንዚን መወደድ፣ የትራንስፖርት ችግር፣ በሠላም ሰርቶና ገበያውን ሸምቶ፣ ጸልዮ፣ ነግዶ፣ ተምሮ፣ እቁብ ጥሎ፣ ዕድር ከፍሎ፣ እንደ ድሮ ተዝናንቶ በሠላም ወደቤት መመለስ እንደማይታሰብ መታወቅ አለበት፡፡ የሚያማምሩ የከተማችን ሕንጻዎች እንዳማረባቸው አይቆዩም፡፡ የኤሌትሪክ፣ የውሃ፣ የስልክ፣ የኔትዎርክ አቅርቦት፣ ሁሉም የየራሳቸውን ችግር ቀርቅበው ይርመሰመሳሉ፡፡

በቦታው >>› ጦርነት፣ ስደት፣ እረሃብ፣ እየተቧደኑ ዝርፍያና መጨካከንን አስከትሎ፣ ማንም አሸንፎ የበላይነት ሳይቀዳጅ፣ ሁሉም ተሸናፊ ይሆናሉ፡፡ “የማን ቤት ፈርሶ የማን ሊበጅ፣ የአውሬ መፈንጫ ይሆናል እንጂ” የምንለው “አይበገሬነት” በተግባር ይተረጎማል፡፡ ከዚያን ቦኋላ ሀገራችን በተባበሩት የዓለም ወይም የአፍሪካ የሠላም አስከባሪ ስር መተዳደር ትጀምራለች፡፡ ሌሎች ችግር ላይ እንደወደቁ ሀገሮች ተራው የኛ ይሆናል፡፡ የዓለም መገናኛዎች በየድኅረ ገጾቻቸው ዜናውን ይዘሩታል.....ወዘተ፡፡

ሁሉም ማታ ሲተኛ ለትራሱ የሚነግረው ስጋትና ተሰፋ እንደመኖሩ፣ ብዙ ሰዎች ይህን በግልጽ አይናገሩም እንጂ የውስጥ ስጋታቸው ነው! አንደባበቅ! ይህ ቀውስ እንዲደርስ ተግተው የሚሰሩ እንዳሉ በእጅ ጣቶቻችን መሃል አጮልገን ሳናይ እውነቱን እንጋፈጥ!፡፡

እነኚህ አደጋዎች በሀገራችን ዙሪያ ተከስተው፣ አጠገባችን የመንና ሶማሌ ላይ ደርሰው ማነው ባለተራ? እያለ ወደ እኛ የሚያማትር ይመስላል፡፡ የቀውስ ዓለማቀፋዊ ተመራማሪ ድርጅቶች ሳይቀሩ አደጋው ሊከሰት እንደሚችል ምልክቶቹን ተናግረው ደጋግመው መክረው አስጠንቅቀዋል፡፡ በዚህ ሙያ ልምድ ያላቸው የሀገራችንም ጠበብቶች ብዙ ምልክቶች ተናግረው አሳስበዋል፡፡

እዚህ ላይ በደንብ ልንረዳ የሚገባን በውስጥ ክፍፍል ላይ ስንተራመስ፣ በዙርያችን ያሉ የጥቅም ተቀናቃኝ ጎረቤቶቻችን፣ የረዥም ጊዜ የይገባናል ፍላጎታቸውን ለማስጠበቅ አድፍጠው አለን ብለው ለሚያልሙት የመሬትና የወሃ ጥያቄ፣ ሁኔታው በቀላሉ በሃይል ለመውሰድ ያመቻቸዋል። እንደ ግብጽ አይነቶች ደግሞ ትርምሱ እንዲስፋፋ የፈለገውን ያህል ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡ በተለይ በእምነት አክራሪነት ለሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ሠርግና ምላሽ ይሆንላቸዋል።

ሃያላን መንግስታት በቀውስ ውስጥ ብሔራዊ የረዥም ጊዜ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ፣ እንደተራ ዜጋ የማናስተውላቸው፣ ብዙ የተደበቁ ፍላጎቶች ስላሏቸው፣ የሚያጧጡፏቸው ንግዶች፣ የሚጸድቁ የረዥም ጊዜ የኤኮኖሚ ስምምነቶች፣ የመሳርያ ሽያጮች፣ የሚካሄዱ ስውር ሹም ሽረቶች፣ እከክልኝ ልከክልሆች ብቻ ሳይሆኑ፣ በዚህ ቀውስ የሚያተርፉና እንደ ሀገር የምንከስርም እዚህ ውስጥ ሳንወድ አለንበት፡፡

ይህ የሃያላን መንግስታት ሀገራትን እየጨፈለቁ በሚፈልጉት መንገድ እንደገና ጠፍጥፈው ለመስራት ያቀዱት የሚመስል ቀውስ፣ ሁሌ መግቢያ ወይም መተላለፊያ አድርገው የሚገለገሉባቸው፣ የስልጣንና የጥቅምና ፍላጎት ያሳበዳቸውን አክራሪ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን እንደ መሳርያ ተጠቅመው የእርስ በእርስ ግጭት ከውስጥ በማስነሳት ነው፡፡ የሁሉም የግጭቶች አነሳስ የተለያየ እንደመሆኑ፣ ወደ እኛም ለመዝለቅ አግኝተው ሊጭኗቸው ያዘጋጅዋቸው መጓጓዣዎች ለስልጣን የቸኮሉ አክራሪ ብሔርተኞችን ይመስላል፡፡

ክልላቸውን ድንበር ለማድረግ “የኛ አይደሉም” የሚሉትን ከየአካባቢው እያስወጡ፣ የየራሳቸውን “ሕገ መንግሥት” በአፋጣኝ እያዘጋጁ ጌቶቻቸው ተበተኑ የሚለውን ፊሽካው እስከሚነፉ በተጠንቀቅ ላይ ናቸው፡፡ ፊሽካው ከላይ የጠቀስኩት ብሔርንና ኃይማኖትን ያስቀደመ ምርጫ እንዳይሆን ያሰጋል!፡፡

ይህ ሂደት እንቅፋት እንዳይገጥመው፣ በቅድሚያ ታስቦበት የተዘጋጀው የሀገሪቷን ሕገ መንግስትና መለያየትን የሚያበረታቱ አንቀጾች፣ እንዳይቀየሩ፣ እንዳይሸራረፉና እንዳይነኩ ዛሬም በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በፌደራል ደረጃ ጥበቃ እየተደረገላቸው ነው፡፡

ይህ በኛ ሀገር አይደርስም፡፡ እኛ ልዩ ሕዝቦች ነን፡፡ ፈጣሪ ስለሚወደን ሀገራችን ምንም ክፉ ነገር አያገኛትም እያልን የራሳችንን ሃላፊነት ወደ እሱ ገፋ እናደርገዋለን፡፡ ጌታ ፀሎታችን የሚሰማው አመዛዝነን እንድንወስን የሰጠንን ኅሊና ተጠቅመን እራሳችንን ስንጠብቅ ነው፡፡

ፈጣሪ የሚረዳን እኛም ስንተባበረውና ቃሉን በማክበር እሱ በቸረን ተፈጥሮ ስርተን መጠቀም ስንችል ነው፡፡ "ይህ በኛ አይደርስም አታሟርቱ!" ብለው ሳይጠነቀቁ ከፈረሱ ሀገሮች ትምህርት ካልወሰድን፣ የፈራነው ደርሶ ከባድ ዋጋ ከከፈልን ቦኋላ ይሆናል የሚገባን፡፡ ያኔ ደግሞ ሁኔታዎች እንደነበሩ ለመመለስ ቀላል አይደለም፡፡ ምናልባት እንኳን ቢቻል፣ እጥፍ ኪሳራና ዋጋ ያስከፍላል፡፡

አክራሪ ብሔርተኞች፣ እውቀት ጉልበትና ገንዘባቸውን አቀናጅተው ሊያፈርሱን ሲጥሩ፣ በምኞትና በፍላጎት ብቻ ሀገራችንን ልናድን አንችልም፡፡ ያውም የልብ ልብ ተሰምቷቸው ምንም ሳይደብቁን ባጭር ጊዜያት ውስጥ ሊጭኑብን የሚፈልጉትን ዝርዝር አጀንዳቸውን በአደባባይ መድረክ ላይ ወጥተው በፉከራ እየነገሩን፣ እኛ በራሳችን ትናንሽ ችግሮች ዙርያ መሽከርከሩ፣ ፍርሃት ወይም "አፍዝ አደንግዝ ምትሃት" እንዳልተደገመብን እርግጠኛ አይደለሁም፡፡

አንዳንድ ተቃዋሚዎች በ2005 ምርጫ ጊዜ ተከስተው በነበሩት ልዩነቶች፣ በግል ጉዳይ ቂም የተያያዙ እስከሚመስሉ፣ አሁንም ከፊት ለፊታቸው እየመጣ ያለውን ጎርፍ ማየት እስከሚሳናቸው፣ ዛሬም አንዱ ከሌላ መሻሉን ነጥብ አስቆጥሮ ለማስመስከር ጊዜያቸውን ሲያባክኑ ከማየት በላይ አሳዛኝ ነገር የለም፡፡ ከራሳቸው ዙርያ ወደ ውጭ ማየት የተሳናቸው እስከሚመስሉ፣ አሁን እያደረጉ ያሉት የእርስ በእርስ ሽኩቻ ከጊዜው ጋር የማይመጥን ሃላፊነት የጎደለው እንደሆነ መረዳት ከብዷቸዋል፡፡ በየጊዜው የሚያገኙትን የሚድያ አውታር የየራሳቸውን ማንአህሎኝነት ለማግዘፍና ተሽሎ ለመደነቅ ከመሞከር ባሻገር እየመጣ ያለውን አስቸጋሪ ሁኔታ የገባቸው አይመስልም፡፡ ወይም ግድ አልሰጣቸውም፡፡

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ በየክልሉ በሚተላለፍ ሚዲያ፣ ሀላፊነት በጉደለው ሁኔታ የሚያሰሙት መልእክት ምንድነው? በብሔር ስም የተከፈቱ በጣም አክራሪ የቴሊቪዥና ራድዮ ጣቢያዎች የሚረጩት ቅስቀሳና እያስከተለ ያለው አደጋ እንዴ ት ነው የምንመለከተው? መንግሥትስ ለምንድነው ዝም ብሎ የሚያያቸው?

ወገኖቼ ሩዋንዳ ላይ የደረሰውን ኢንተርሃሞይ የቀሰቀሰው አንድ ራድዮ ጣቢያ ነው፡፡ ጋዜጠኝነት አንዱ ከሌላው መሻሉን ለማስመስከር፣ ወይ መንግሥትን እስከ ጥግ ሄዶ ካለገደብ መደገፍ፣ አሊያም በጎ ነገር ላለማየት ምሎና ተገዝቶ የመንግሥትን አሉታዊ ገጽታን ብቻ ከተቃዋሚ ብሶ አጨልሞ ለማሳየት መሟሟት ሁለቱም ጨለምተኛነት ነው፡፡ ምነው ሙያውን ቢያከብሩ?፣ እንደዚህ ጎራ መርጠው የግል ጸብንና የቂም በቀል መወጣጫ ባያደርጉት?፡፡ ተቃዋሚ ሊሳሳት፣ መንግስትም በጎ ነገር ሊሰራ ይችላል፡፡ እባካችሁ ከግል ስሜትና ፍላጎት እርቃችሁ ሚዛናችሁን ጠብቁ፡፡ መንግስትን ለመቃወም ወያኔን መደገፍም ሆነ የተገላቢጦሽ፣ ሁለቱም ስህተት ነው፡፡ ከምንቃወመው ነገር ተሽለን እንገኝ፡፡

ትክክልም ይሁን የተሳሳተ መረጃ፣ በወያኔ አስተናጋጅነት እየተሰባሰቡ ያሉት የጎሳ ፌደራሊስቶች፣ የወያኔን የቀድሞ አስተዳደርን ለመመለስ፣ ከባድ ልዩነቶቻቸውን ጭምር አቻችለው ብዙ ድርጅቶች ሆነናል እያሉን ነው፡፡ ይንን ዓላማቸውን ለማሳካት፣ ባዳበሩት ድርጅታዊ ተንኮልና ልምድ፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም፣ በተቀነባበረ መንገድ ሲዘርፉ የኖሩትን ገንዘብ እንደ ጉድ እየረጩ ጠንክረው ሲሰሩ ተደብቀው አይደለም፡፡

ታዲያ ይህ አይነት <u>የባሰ አደጋ</u> ከፊታችን ተደቅኖ፣ አሁንም ድሮ በነበሩ ሽኩቻዎች ውስጥ ተውጠው፣ "ማን ልክ ነበር?" የሚለውን ለማስመስከር ሲደናበሩ፣ ሁሉንም ቀርጥፎ የሚውጥ ዘንዶ እየቀረባቸው እንደሆን እንዴት ማስተዋል ተሳናቸው?፣ ወይስ አንዳንዶቹ ሆን ብለው ይህንን መከፋፈል ወጥረው በማራገብ፣ ወያኔን የሚቃወሙት አብረው እንዳይቆሙ የተሰጣቸው የሥራ ድርሻ ይሆን?፡፡

ማንኛውንም መንገድ ተጠቅመው ሀገርን በማፍረስ ያመለጣቸውን ስልጣን ለመመለስም የሚፈልጉትም ሆኑ፣ አዲሶቹ ተረኞች ወደ ስገነቱ ለመውጣት እየተሟሟቱ ያሉት ሁለቱም መርኅ አልባ ኅብረት ፈጥረው

እየተቀናጁ እንዳሉ ማየት አያስቸግርም፡፡ እነዚህ የጋራ ዓላማ ሳይሆን "የጋራ ጠላት" አለን ብለው፣ ለቆሙለት ዓላማ ተግባር ያስተሳሰራቸው፣ ነገ አብረው እንደማይዘልቁ ቢታወቅም፣ አብረው ሀገርን ለማፍረስ አይችሉም ብሎ መዘናጋት የዋህነት ነው፡፡ የቅርብ ትዝታችንን ወያኔንና ሻቢያን እናስታውስ፡፡ ዛሬም እንደዚህ አይነት ብዙ "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" ትውልድ አክሳሪ ጊዜያዊ የውሸት "ትብብር" እየተደገመ ነው፡፡ ምናልባት ካልዘገየን? ይህን አደጋ ተከላክለን ሀገራችንን ከቀውስ በማዳን ዜጋዊ ግዴታችንን መወጣት ካልቻልን፣ "ከወደቁ ወዲያ መፈራገጥ ለመላላጥ" ነው የሚከተለው፡፡

በተበታተነ መንገድ፣ በብሔርና በዕምነት ዙርያ እየተቧደኑ ስሜትን ብቻ በመኮራኮር በማይጨበጥ ተስፋ መመርቀን ማቆም አለብን፡፡ ካሁን በኋላ አንድ ብሔር፣ (ኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግሬ..ወዘተ) ብሎ በመሰባሰብ፣ ወይም በአንድ ዕምነት ዙርያ ብቻውን ተደራጅቶ ኢትዮጵያን አስተዳድራለሁ፣ ወይም ኢትዮጵያን ብቻዬን አድናለሁ የሚል በተግባር ሊተረጎም የማይችል ተስፋ መቆም አለበት፡፡ እንደዛ እንድናምን አሁንም የሚደክሙ ካሉ? ወይ ያልገባቸው አሊያም ሌላ የራሳቸው "ባወጣ ያውጣን" የሚሉ የግላቸው አጀንዳ ያላቸው ብቻ ናቸው፡፡

በእውነት የኢትዮጵያን ህልውና እንዲቀጥል ለሚፈልጉ፣ እንኳን ለየብቻ በኅብረትም ቀላል አይሆንም፡፡ ተቀራራቢ ሀገራዊ አጀንዳ ያላቸው የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ድርጅቶች፣ ወደ አንድ አቅጣጫ ተሰባስበው፣ እየመጣ ያለውን አደጋ በጋራ የማክሸፍ ተግባር ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ አቢይ ጉዳይ ነው፡፡ ወደፊትም እነዚህ አጥፊዎች የጀመሩትን ዓላማ ግብ ለማድረስ፣ በስልት የተቀነባበረ የሕዝባችንን የእይታ አቅጣጫ ለያስቱ የሚችሉ ብዙ አሰቃቂ ችግሮች እንደሚሞክሩ አንዘንጋ፡፡ ባለፉት ጊዜያት በፍጥነት እያደጉ የመጡት፣ ግድያዎች፣ መፈናቀሎች፣ አፈናዎች እና የአክራሪ ብሔረተኞች ጭፍን የጥላቻ ቅስቀሳዎች ወዴት ሊያመሩ እንደሚችሉ አባነው አንቅተውን አብረን ሊያስቆሙን ካልቻሉ? በራስ ቀቢጸ ተስፋ በራሳችን የህልም ቅዠት ውስጥ ተውጠን በመመርቀን እየቀረበ ያለውን አደጋ እንዳናይ ጋርዶብናል ማለት ነው፡፡

ሀገርን ጽንፍ ከቆሙ ከአክራሪ ብሔርተኛ ድርጅቶች፣ እያካሄዱ ካለውና ወደፊትም ሊፈጥሩ ከሚችሉት ቀውስ ለመከላከል፣ ከሀገር ውስጥ እስከ ዲያስፖራ፣ ጉዳዩ ያሳስበናል የሚል ማንኛውም ዜጋ፣ ኃይማኖት እና ጥቃቅን የፖለቲካ ልዩነቶች ሳይከፋፍለው፣ ከምንም ነገር በፊት በቅድሚያ ለጋራ ችግራችን በያለንበት እተሰባስበን ሰከን ብለን በመወያየት መፍትሄ የምንፈልግበት የመጨረሻ ሰአት ላይ ነን፡፡

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የክርስትና፣ የእስልምና እና የሌሎችም እምነት የኃይማኖት አባቶችና እናቶች፣ ሀገር ውስጥ ብዙ ቦታዎች ኮሚቴ አቋቁመው አብረው በመቆም በእምነቶቻችንና በማኅበራዊ ጥቅሞቻችን ዙርያ ለደረሱት እኩይ ተግባሮች ተቃውሚቸውን በጋራ እያከታተሉ እንዳስተላለፉት፡፡ እነዚህ ከሁሉም ማእዘን የተወጣጡ የእምነት አባትና እናቶች፣ እንዲሁም ጉዳዩ ያሳሰባቸው ዜጋዎች፣ ችግር ፈጣሪዎቹ እንደተመኙት ሳይከፋፈሉ፣ እንዲያውም አብረው ይበልጥ ተቀራርበው እየተመካከሩና እየተረዳዱ ቀውስ ፈጣሪዎቹን ባደባባይ አውግዘው አሳፍረዋቸዋል፡፡ ይህ እርምጃ የብዙ ቀውስ ቀስቃሾችን ቅስም ሰብሯል!፣

ባጭሩ ሀገራችን የገባችበትን የችግር ክብደት በማጤንና የአባት/እናቶቻችንን ፈለግ በመከተል፣ ከግል አላስፈላጊ እሰጥ አገባዎች ሻገር በማለት፣ በተለያየ ምክንያት ሁኔታው አስገድዷቸውም ሆነ እራሳቸውን ለመከላከል ወደ ጠርዝ ወጥተውም የነበሩትም ጭምር ወደ መሃል በመምጣት በሀገራችን አሳሳቢ ጉዳዮች ዙርያ ባስቸኳይ እየተሰባሰብን በመምከር የሃላፊነት ድርሻችንን እንወጣ፡፡

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ከጥንፈኛ መራጮች እና ከጅል ተፎካካሪዎች ይሰውራት!

tebaber@gmail.com